# ዓለምና ጊዜ

ዓለም ከርታታ ነች እንደየ ዘመኗ
ጊዜን ወዳጅ አርጋ አቁማ ከጎኗ
ግን ያነገሰችው ውሎ አድሮ ሲነጋ
ክብር የነበረው ድንገት ያጣል ዋጋ።

# ባርነቱ

ጨለማ ፅልመቱ ብርሃን አጥቶ
ሰላም እርጋታዋ በጦርነት ሙቶ
የዳኝነት ፍርዱ ፍትሁ ተዛብቶ
ዕውነትን ሞግቶ ሀሰት ረትቶ
ስብዕና ተላብሶ ሰው በሰውነቱ
መኖሩ አይታይም ጎልቶ ባርነቱ።

# ኖርንና

ጭብጥ ጥሬ በልቶ
ጥርኝ ውኃ ጠቶ
ኖርኩ እንዲልም ኑሮ
የደከመ አካሉን መደብ ላይ ዘርሮ፤

የበሽታ ቀለብ የሞት ስንቅ መኖ
የርሃብ ከረጢት አይጠግቤ ለምኖ፤

እጆቹን ዘርግቶ አንጋጦ ወደ ላይ
ተመስገን ጌታየ ይህን አታሳጣይ
ለሚል ምጿተኛ ልቡ ደምቶ አዶናይ፤

ቸርነት ካልቸረው መዳህኔዓልም ደጉ
ማተብ ያስበጥሳል ድርጊተ-ፈለጉ።

# ዋቶ አደር

አማራና ጦቢያ ተስለው ባንድነት
ወሎን በአጋሜ፣ ጎንደርን በቅማንት
ሸዋን በኦረሞ ቂምና ብቅላት
ጎጃምንም በአገው፣ አማራን ለማጥፋት
ፖሊሲ ተቀርፆ ዘር ማፅዳት ትግብርቱ
ከዳር እስከ መሃል ሲለኮስ እሳቱ
ምነው ቤተ-አማራ አለመዋተቱ?

ሚያዚያ 2008